QuickNotes mcps በአማርኛ

**October 3, 2018 QuickNotes**

## የትምህርት ቤት "Open Houses" ፕሮግራም ኦክቶበር 8 ይካሄዳል

ኦክቶበር 8 በሚካሄደዉ Open House ወቅት የትምህርት-ቀን ከልጅዎ ጋር አብረው ያሳልፉ።

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) **ሰኞ፣ ኦክቶበር 8** ት/ቤቶች "open houses" የሚያካሄዱበት ቀን እንዲሆን ተሰይሟል። ልጆቻቸውን በመማርያ ክፍል ውስጥ ለመታዘብ፣ ስለትም/ቤቱ ፕሮግራሞች ለመማርና የትም/ቤቱን መምህራንና ሰራተኞችን ለማግኘት፣ ይህ ለወላጆች ትልቅ እድል ነው። ለተጨማሪ መረጃ ከልጅዎ ት/ቤት ያጣሩ።

## Bannockburn እና Luxmanor የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ 2018 National Blue Ribbon ት/ቤቶች በመባል ተሰይመዋል።

የ National Blue Ribbon ፕሮግራም፤ የላቀ አካደሚክ እና የስኬታማነትን ክፍተት መዝጋት ለቻሉ ት/ቤቶች እውቅና ይሰጣል።

Bannockburn እና Luxmanor አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ 2018 "National Blue Ribbon Schools" በመሆን በ ዩ.ኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት ተመርጠዋል። የሽልማቱ አሸናፊዎች ማስታወቂያ የተገለጸው ኦክቶበር 1 ነው።

የ National Blue Ribbon program በአጠቃላይ የላቀ የትምህርት ስኬታማነታቸዉ ወይም በተማሪዎች ንዑስ ቡድኖች መካከል ያለውን ክፍተት ለማጥበብ በሚያሳዩት የመሻሻል እርምጃ ላይ በመመስረት ለህዝባዊ እና የግል ት/ቤቶች እዉቅና ይሰጣል። በነዚህ ት/ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎች በምንባብ እና በሂሳብ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ከመሆናቸውም በላይ አብዛኛዎቹ ት/ቤቶች በኤኮኖሚ አቅም ዝቅተኛ የሆኑ ተማሪዎችን የሚያገለግሉ ናቸው። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የ "National Blue Ribbon Schools" ስያሜ ከተጎናጸፉት መካከል Bannockburn እና Luxmanor 40ኛ እና 41ኛ ት/ቤቶች ናቸው። እያንዳንዱ የ2018 National Blue Ribbon ት/ቤት ከጠቅላላ የሜሪላንድ ት/ቤቶች በ2017 የስቴት ምዘና ውጤት ከፍተኛ 15 ፐርሰንት ውስጥ ያሉ ናቸው።

ሁለቱም ት/ቤቶች በዲሴምበር 2017 የሜሪላንድ "Maryland Blue Ribbon Schools" በመባል የተሰየሙ ሲሆን፣ ይህም ለአገር-አቀፉ "National Blue Ribbon Schools" እንዲታጩ አስችሏቸዋል። ሌሎችም ከስቴቱ በአሸናፊነት ብሔራዊ ክብር የተጎናጸፉት፡- ዌስት ታውሰን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት - West Towson Elementary School፣ ከባልቲሞር ካውንቲ/Baltimore County፣ ኡርባና አንደኛ ደረጃ ት/ቤት/Urbana Elementary School፣ ከፍሬድሪክ ካውንቲ/Frederick County፣ ፎልስተን መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት/Fallston Middle School፣ ከሃርፎርድ ካውንቲ/Harford County፣ እና ዋተርሉ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት/Waterloo Elementary School፣ ከሃዋርድ ካውንቲ/Howard County ናቸው።

ባንኩበርን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (Bannockburn Elementary School) በሜሪላንድ ስቴት የ 4ኛ ክፍል (ELA/4) የ2017 በ PARCC የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ ከፍተኛ ዉጤት ያስመዘገበ ተብሎ ተሰይሟል። ትምህርት ቤቱ ከተማሪዎቹ ውስጥ 89 በመቶ በላይ ያህሉ በሒሳብ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ስነ-ጥበባት ከሚጠበቀዉ ወይም ከሚጠበቀዉ በላይ የ PARCC አማካይ ውጤት አላቸው። በ2016፣ ባንኩበርን/Bannockburn የተረጋገጠለት አረንጓዴ ት/ቤት (Certified Green School) ሁኗል። ከወላጆች ጋር ጠንካራ ወዳጅነት/ሽርክና ከመገንባቱም በላይ የ PTA አባልነት የተሳትፎ መጠን በየዓመቱ በአማካይ ከ80 ፐርሰንት በላይ ነው። በአስተማሪዎችና በተማሪዎች ላይ ተጽእኖ የሚፈጥሩ እንደ የመሥራት ፍላጎትን/አስተዋይነትን ፕሮግራምን ጨምሮ፣ ቀጣይነት ባለው ሙያዊ/ፕሮፌሽናል እድገት አማካኝነት አቅምን ለማጎልበት ሠራተኞች በቁርጠኝነት ይሠራሉ። Bannockburn ለሁሉም ተማሪዎች እድገት ላይ የሚያተኩር ስልቶች/ስትራተጂ ለማረጋገጥ በመምህራን የሚመሩ የመረጃ ውይይቶችን ለማመቻቸት የእድገት ቦርድ አቋቁሟል። በተደጋጋሚ የሚነገረውከሁሉ የበለጠ ማስተማር የመጀመሪያው ማስተማር ነውሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች በአነስተኛ ቡድን ተለይተው የማስተማር ሁኔታ አስረጂ ነው።

ለክስማኖር (Luxmanor) አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ22 አገሮች የመጡ 26 ፐርሰንት ተማሪዎች ልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ የተማሪ ማህበረሰብ አለው። ለክስማኖር/Luxmanor ከት/ቤቱ ማህበረሰብ 13 ፐርሰንት የያዘ የልዩ ትምህርት ፕሮግራሞች ባለቤት ነው። ሆኖም፣ በ45 ፐርሰንት የጥቅም ጉዳት/የሚጎዳ ነገር ያለባቸው ተማሪዎችን ይዞ፣ ለክስማነር/Luxmanor በሂሳብ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነ ጥበብ በአማካይ ከ65 ፐርሰንት በላይ ተማሪዎች የሚጠበቀዉን ወይም ከሚጠበቀው በላይ ውጤት አምጥተዋል። ከመማሪያ ክፍል ያለፈ፣ በዓመታዊው የምግብ፣ የአልባሳት፣ የት/ቤት ቁሳቁሶችና ገንዘብ በማሰባሰብ ተማሪዎቹ የሚያደርጉት ጥረት በማህበረሰቡ ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ አሳድሯል። የት/ቤቱ የኃይል እና መልሶ አገልግሎት ላይ የማዋል ቡድን ት/ቤቱን ለሜሪላንድ የአረንጓዴ ት/ቤት ማረጋገጫነት አስተዋጽኦ አድርጓል። እንዲሁም ለክስማነር/Luxmanor የ 2017–2018 የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ MCPS ለዓመቱ መምህርነት ለፍጻሜ የደረሰች ተወዳዳሪ - ለ Melissa Segal ት/ቤቷ ነው። በመደበኛው እና በልዩ ትምህርት ተማሪዎች መካከል የሚካሄድ የተማሪ መካሪ-አሰልጣኝ ግንኙነቶች በት/ቤቱ ድጋፍ ይካሄዳሉ።

ባኖክበርን/Bannockburn፣ ለክስማነር/Luxmanor እና ሌሎችም ተከባሪዎች ኖቬምበር 7 - 8 በዋሽንግተን ዲ.ሲ (Washington, D.C) በሚካሄዱት ሥነሥርአታዊ በአል የከበሬታ እውቅና ይሰጣቸዋል።

[ብሔራዊ የብሉ ሪባን ትምህርት ቤቶች/National Blue Ribbon Schools]

[ባኖክበርን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Bannockburn Elementary School]

[ለክስማነር አንደኛ ደረጃ ትምህት ቤት/Luxmanor Elementary School]

**በዓመታዊ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ሣምንት ላይ ይሣተፉ**

ከኦክቶበር 21 - 28 በሚካሄደው በዓመታዊ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ሣምንት ላይ በመሣተፍ ወላጆች እና ተማሪዎች በማህበረሰቦቻቸው ዉስጥ ተጽእኖ ለመፍጠር ይችላሉ።

በጠቅላላ በካውንቲው ውስጥ በርካታ በጎ ፈቃደኞች የሚሣተፉበት ከኦክቶበር 21 - 28 የሚካሄደው 32ኛው የሞንትጎመሪ ካውንቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ሣምንት እድሎች ላይ ለመሳተፍ ይዘጋጁ። ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሰአቶች መመሪያዎችን የሚያሟሉ በርካታ ፕሮጀክቶችን ጨምሮ፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ሣምንቱን በሙሉ በአካባቢ የሚገኙትን ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶችን፣ ት/ቤቶችን፣ እና የመንግስት ኤጀንሲዎችን በማገልገል ለመርዳት የሚያስችላቸው በርካታ መንገዶች አሉ።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ (Montgomery County) የበጎ-ፈቃደኛ ማእከል መስመር ላይ የበጎ-ፈቃደኛ ፍላጎቶች ቀን መቁጠርያ የወቅታዊ የፕሮጀክቶች ዝርዝርን ይቆጣጠሩ/ይመልከቱ (ፕሮጀክቶች በየእለቱ ስለሚጨመሩ በየወቅቱ መልሳችሁ ተቆጣጠሩ/ይመልከቱ)፣ እናም ፍላጎታችሁን የሚያሟሉ ማንኛውንም ወይም ሁሉንም ያንሱ/ይቀበሉ።

እርስዎ ለመሣተፍ ከሚፈልጉት የትልቅ ቡድን አካል ከሆኑ፣ ወይም ፕሮጀክት ለማስተናገድ የሚፈልግ ለአትራፊነት ያልተቋቋመ ድርጅት (ት/ቤት ወይም PTA ጨምሮ) ጋር ግንኙነት ካለዎት እንዴት ለመሳተፍ እንደሚችሉ ለማወቅ ኢ-ሜይል servicedays@montgomerycountymd.gov ወይም የበጎፈቃድ ማእከልን በስልክ ቁጥር፦ 240-777-2600 ደውለው ይጠይቁ።

## **ዎርልድ ኦቭ ሞንትጎመሪ ፌስቲቫል  የተለያዩ ባህሎችን-ብዙሃነት ያከብራል**

እሁድ ኦክቶበር 21 ከእኩለ ቀን ጀምሮ እስከ 4 p.m በሞንትጎመሪ ኮሌጅ ሮክቪል ግቢ/Montgomery College's Rockville campus ስለሚካሄድ ይህ ዓመታዊ ዝግጅት እንዳያመልጥዎት ቀጠሮ ይያዙ። ዝግጅቱ ነፃ እና ምግብ፣ ሙዚቃ፣ ዳንስ እና መስተጋብራዊ እንቅስቃሴዎችን ለጠቅላላ ቤተሰብ ያቀርባል።

የሞንትጎመሪ - (Montgomery) ዎርልድ ፌስቲቫል የሞንትጎመሪ ካውንቲ (Montgomery County) እና የዋሺንግቶን፣ ዲ.ሲ. አካባቢ የበለፀገ/የደለበ ባህላዊ ቅርሶችን ያከብራል ትርኢይትም ያሳያል። በአሉ የሚካሄደው **እሁድ፣ ኦክቶ. 21**፣ በሞንትጎመሪ (Montgomery) ኮሌጅ ሮክቪል ካምፐስ፣ 51 Mannakee Street in Rockville፣ ከቀትር እስከ 4 p.m. ነው።

በዚህ አመት በአል MCPS ሸርከኛ/ተባባሪ በመሆኑ ይኮራል። ነፃው ክውነት የሚያካትታቸው አለማቀፍ መንደር፣ አለማቀፍ ወጥ ቤት ከባህላዊ ምግብ ትእይንት በዋና ወጥ ቤት፣ የእጅ ስራ ገበያ፣ የባህሎች ሰልፍ፣ ሁለት የባህላዊ ጭፈራና ሙዚቃ መድረኮች፣ በአገልግሎቶች ግንኙነቶች፣ ባህላዊ ኪነጥበባት፣ እና ጨዋታና የእርስበርስ እንቅስቃሴዎች ለሞላ ቤተሰብ። ለተጨማሪ መረጃዎች፣ www.worldofmontgomery.com ይጎብኙ።

## **ለተማሪ የመሪነት እድሎች አሉ**

Maryland Student Page Program/የሜሪላንድ ተማሪ ፔጅ ፕሮግራም በአናፖሊስ ለሚካሄደው የ2019 ሜርላንድ ፓርላማ ክፍለ ጊዜ (ጀንዩወሪ-ኤፕረል) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ይፈልጋል። ቢያንስ 16 አመት የሞላቸው የሜሪላንድ የከፍተኛ ዓመት ተማሪዎች ለማመልከት ብቁ ናቸው። ፕሮግራሙ የታለመው ለሚከተሉት ነው፡-

1. በስቴት አስተዳደር የወጣቶችን ፍላጎት ለማነሳሳት፣
2. በአስተዳደር ተሳትፎን ለመጨመርና በወጣቶች መካከል አመራርን ለማሳደግ፣ እና
3. ሕግ አውጭዎችና ሌሎች ሹማምንት ጋር በመገናኘት፣ ተማሪዎች ወሳኝ አገልግሎት ለህግ አውጪ አካል እንዲያቀርቡ ማስቻል።

ፔጆች/ተማሪዎች በሰኔት ወይም በሃውስ ኦፍ ደለጌትስ ለ13 ሳምንቶች ይመደባሉ ለያንዳንዱ ያገለገሉበት ቀን $55 የኪስ ገንዘብ ይሰጣቸዋል። ማመልከቻ ለማቅረብ የጊዜ ገደብ **ዓርብ፣ ኦክቶበር 26 በ 5 p.m** ማመልከቻዎች በድረ-ገጽ ላይ ይገኛሉ።

## **የሞንትጎመሪ ኮሌጅ የወደፊት የኮሌጅ ተማሪዎች FAFSA በመሙላት ለመርዳት ዝግጅት አለው**

በዚህ ዝግጅት ኮሌጅ የሚገቡ ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው FAFSA ቅጽ/ፎርም ለመሙላት የባለሙያ/ፕሮፌሽናል ድጋፍ ለማግኘት ይችላሉ።

የ2019-2020 Free Application for Federal Student Aid/ለፌደራል የተማሪ እርዳታ (FAFSA) ነፃ ማመልከቻ የቀረበው ኦክቶበር 1/2018 ነው። ኮሌጅ የሚገቡ ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው FAFSA ፎርም ለመሙላት በሁለተኛው ኣመታዊ FAFSA Fever/በሚጋጋልበት ወቅት ፎርሙን ለመሙላት ሙያዊ ድጋፍ ለማግኘት ይችላሉ። ይህ ዝግጅት የሚካሄደው በሞንትጎመሪ ኮሌጅ ግቢ ውስጥ የተማሪ ፋይናስ ድጋፍ ጽ/ቤት እሁድ ኦክቶበር 14 ቀን ከ12 - 3 p.m በታኮማ ፓርክ ሲልቨርስፕሪንግ ካምፓስ/Takoma Park/Silver Spring Campus in the lobby of the Charlene R. Nunley Student Services Center ይሆናል። ፓርኪንግ በ East Garage በኩል ይገኛል።

FAFSA Fever ቤተሰቦችን FAFSAን—ለስኮላርሺፖች፣ የገንዘብ ስጦታዎችና ብድሮች ለማግኘት ብቃት ለማግኘት በ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ተፈላጊ ፎርም—ሲሞሉ የሚያግዛቸው ክውነት ነው። FAFSA ፊቨር/በሚጋጋልበት ወቅት በነፃ ለህዝቡ ክፍት ነው። በዚህ ወቅት የኮሌጅ ተማሪ የሆኑና FAFSA ለማሳደስ የሚፈልጉ ወይም ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚጠይቁ በዚህ ዝግጅት መሳተፍ ይችላሉ።

ተማሪዎች እና ወላጆች FAFSA በኢንተርኔት/online በሚሞሉበት ጊዜ የፋይናንስ እርዳታ ባለሞያዎችን ለማግኘት እድል ይኖራቸዋል፣ እንዲሁም የሞንጎመሪ ኮሌጅ ኮምፒውተር ላብ ለመጠቀም ይችላሉ። በዚህ ወቅት የሞንጎመሪ ኮሌጅ ተማሪዎች የሆኑ $500 ስኮላርሽፕ ለማሸነፍ መግባት ይችላሉ።

የቦታ ውስንነት ስላለ መመዝገብ አስፈላጊ ነው። ለመመዝገብና ማምጣት ያለባችሁን ሰነዶች ሙሉ ዝርዝር ለማውረድ፣ እባካችሁ www.montgomerycollege.edu/FAFSAFever ጎብኙ። Please visit [www.montgomerycollege.edu/FAFSAFever](http://www.montgomerycollege.edu/FAFSAFever) to register and download a complete list of documents to bring.